የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት
# የኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
## የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተመደበለት በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኮሚሽኑ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣንና ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ስልት በመከተል ነው፡፡

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት ) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት እና ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኮሚሽኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያ ናቸው ፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኮሚሽኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት
- የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት

የኮሚሽኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

ወጪ፤

1. ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት መግዛት ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ግዥ በመፈፀሙ በብልጫ ብር 266,406.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
2. ያለውድድር በቀጥታ ለኢንቨስትመንት ጋይድ ብሮሸር ግዥ ብር 346,808.95 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
3. የበጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ብር 744,853.41 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
4. አለአግባብ የአበል ክፍያ ብር 21,000.00 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

5. 37,884.96 ተሰብሳቢው የሚፈለግበትን ድርጅት ወይም ግለሰብ ሥም እንዲሁም ለምን እንደተከፈለ የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ ባለመቅረቡ ሂሳቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
6. ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያልተከፈለ ብር 71,445.69 ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የሂሣብ ሪፖርቶቹ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30/2011 ድረስ የተሰበሰበው ገቢ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን የተከተሉ መሆኑን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች

መደበኛ በጀት ብር 36,836,773.07 (46.88%) ሥራ ላይ ያልዋለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፤

20 ኮምፒተር፣ 10 ፕሪንተር፣ 60 ዩፒኤስ ፣2 ስካነር፣ 20 የተሽከርካሪዎች ወንበር፣ 20 ኤክስፐርት ጠረጴዛ፣ 33 የእንግዳ ወንበር ፣10 ሼልፍ ፣6 የብረት ፋይል ካቢኔት ፣ ጋዜጣ ፣5 ሂተር ፣150 ያገለገሉ ቶነሮች ፣80 ያገለገሉ የመኪና ጎማ እና ያገለገሉ የመኪና መለዋወጫዎች ያልተወገዱ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከሠላምታ ጋር